https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ 201235

ህዳር 28 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፊይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አብዲ አሚን አሊሾ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ሙሳ ኡስማን ዑመር

2ኛ. ወ/ሮ ደሃቦ አብደላ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በቀን 06/05/2013 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 75621 በቀን 14/12/2011 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 16162 በቀን 08/04/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው። ክርክሩ የጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት አቤቱታ ነው።

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች በቀን 03/11/2011 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ በድሬዳዋ አስተዳደር ጀሎ በሊና ገጠር ቀበሌ ልዩ ስፍራው ኢጃነኒ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኝ አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰ 1000 ካ/ሜ በግምብ አጥር የታጠረ ይዞታና ግምቱ 50,000.00 ብር የሆነ መኖሪያ ቤት ያለኝ ሲሆን ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በእውነት በእጄ አድርጌ እያዘዝኩበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እገኛለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ተከሳሾች ምንም አይነት መብት ሳይኖራቸው ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ በይዞታው ላይ በሃይል የተደገፈ ሁከት እየፈጠሩብኝ ይገኛሉ፡፡ በተደጋጋሚ ሁከቱን እንዲያቆሙ በግልም ይሁን በሽማግሌ ባስጠይቃቸውም ሁከቱን ሊያቆሙ ፍቃደኛ ባለመሆናቸው የፈጠሩትን ሁከት እንዲወገድ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት መልስ ክርክር የተነሳበት ይዞታ ተከሳሾችና ቤተሰቦቻችን ለ17 አመት የምንገለገልበት የግል ይዞታችን እንጂ የከሳሽ ይዞታ አይደለም፡፡ አከራካሪው ይዞታ በእኛ እጅ የሚገኝ ራሳችን የምናስተዳድረው ነው፤ ከሳሽ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1140 መሰረት ይዞታውን በእጁ አድርጎ የማያስተዳድረው በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1149 መሰረት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ሊያቀርብ አይችልም፡፡ ከሳሽ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን በቀርሳ ወረዳ ወተር ከተማ ነዋሪ ሆኖ አከራካሪው ይዞታ የሚገኝበት በድሬዳዋ አስተዳደር ጀሎ በሊና በቀበሌ ያለውን ይዞታ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በእጁ አድርጎ የሚይዝበት ምክንያት የለም፡፡ ከሳሽ ከህግም ይሁን ከውል የመነጨ መብት የለውም፡፡ በመሆኑም የከሳሽ ክስ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ከቀረቡት የከሳሽና ተከሳሾች ምስክሮች እንዲሁም ከጀሎ በሊና ገጠር ቀበሌ የመጣው የሰነድ ማስረጃ አንጻር ሲመዘን የእርሻ መሬቱ አመጣጥ የ1ኛ ተከሳሽ የነበረ መሆኑ በኋላ ላይ ግን 1ኛ ተከሳሽ ለከሳሽ በብር 100,000.00 ባዶ መሬት የሸጠለት መሆኑ፤ በዚህም መነሻነት ከሳሽ በግምት 1000 ካ/ሜ የሚሆነውን ከ1ኛ ተከሳሽ የገዛውን ባዶ መሬት በግንብ ያጠረው መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከሳሽ ይህን ከ1ኛ ተከሳሽ የገዛውን ባዶ መሬት ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በግንብ አጥሮ በይዞታው ስር አድርጎ የሚጠቀምበት መሆኑም ተረጋግጧል፡፡ ከሳሽ አከራካሪውን ይዞታ በሽያጭ ውል ከ1ኛ ተከሳሽ ያገኘው መሆኑን ከከሳሽ ምስክሮች የተረጋገጠ በመሆኑ የከሳሽ ይዞታ መብት ከውል የመነጨ መሆኑ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ ከሳሽ ከ1ኛ ተከሳሽ የገዛው መሬት ባዶ መሬት በመሆኑ ህገ መንግስቱን አንቀጽ 40(3) እና የፍ/ብ/ህ/ቁ 1678(ለ) የጣሰ ነው፤ በመሆኑም ውሉ እንዲፈርስ ከተዋዋዬች አንዱ ወይም ማንኛውም ጥቅም ያለው ሰው መጠየቅ እንደሚችል የፍ/ብ/ህ/ቁ 1808(2) አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም ውሉ ፈራሽ ነው፡፡ ከሳሽ አከራካሪውን ይዞታ ያገኘው ህገወጥ ውል መሰረት በማድረግ ስለሆነ ውሉ ከመጀመሪያውኑ እንዳልተደረገ የሚቆጠር ነው፡፡ ህገወጥ በሆነ ውል አማካኝነት የተቀባበሉትን በፍ/ብ/ህ/ቁ 1815(1) መሰረት ከውሉ በፊት ወደ ነበሩበት ሊመለሱ ይገባል፡፡ ከሳሽ በውሉ አማካኝነት ለ1ኛ ተከሳሽ የከፈለው ገንዘብ ብር 100,000.00 ከ1ኛ ተከሳሽ ሊመለስለት ይገባል፣ በምላሽ የተረከበውን መሬት በነበረበት ሁኔታ ለ1ኛ ተከሳሽ ሊመልስ ይገባል፡፡ ስለሆነም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተከሳሾች በህገ ወጥ ውል ወይም በፈራሽ ውል ያስተላለፉትን መሬት መልሰው መያዛቸው የሁከት ተግባር አይደለም፡፡ ሊወገድ የሚገባው ሁከት የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ከሳሽ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም ለክርክር መነሻ የሆነውን ይዞታ በተመለከተ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1140 መሰረት በእውነት የሚያዝበት የይ/ባይ ይዞታ ነው? ይ/ባይ በዚህ ይዞታ ላይ የህውከት ይወገድልኝ አቤቱታ ሊያቀርብበት የሚችል ነው? የስር ፍርድ ቤት ግራቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ በማለት የሰጠው ውሳኔ ከቀረበው ክስ እና ከግራቀኙ ክርክር አንፃር ተገቢ ነው? የሚሉ ጭብጦችን በመያዝ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ ቀበሌው በጉዳዩ ላይ በጻፈው ማስረጃ ይ/ባይ እና 1ኛ መ/ሰጪ በነበራቸው የሽያጭ ውል መሰረት ይ/ባይ ይህን ይዞታ የያዘው መሆኑን ከመግለፅ ውጪ አከራካሪው ይዞታ የይ/ባይ መሆኑን አላረጋገጡም፤ ይ/ባይም በምን አግባብ ይህን ይዞታ የያዘ ስለመሆኑ አላረጋገጠም፤ ቦታው የገጠር መሬት እንደመሆኑም የገጠር መሬት ሊገኝባቸው በሚገኝባቸው መንገዶች ስለመገኘቱም የቀረበ ማስረጃ የለም፤ ቦታው ወደ ከተማ የተከለለ ነው የሚባል ከሆነም አሁንም ይህንኑ ሊያረጋግጥ የሚችል ምንም አይነት ማስረጃ አላቀረበም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይዞታው በሽያጭ የተገኘ ስለመሆኑ ቢገልፅም ህጋዊ የቤት ሽያጭ ውል ስለመኖሩ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ በአጠቃላይ ይ/ባይ በእውነት ሊያዝበት የሚችል የራሱ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ባለመቅረቡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1140 እና 1149 መሰረት ሁከት ይወገድልኝ በማለት አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚችልበት የህግ መሰረት የለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም፡፡ ግራቀኙ ወደ ነበሩበት ይመለሱ በማለት የሰጠውን ውሳኔ በተመለከተ ይ/ባይ በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ሁከት ይወገድልኝ የሚል ሲሆን በመ/ሰጪ በኩልም የቤት ሽያጭ ውል ወይንም የመሬት ሽያጭ ውልን በተመለከተ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ በመሆኑም በሁለቱም በኩል ውልን በተመለከተ የቀረበ ክርክር ባለመኖሩና በፍ/ብ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 182(2) አንጻር ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባው ከተጠየቀው ዳኝነት አንጻር በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ይህን በማለፍ ግራ ቀኙ ወደ ነበሩበት ይመለሱ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም፡፡ በሌላም በኩል የህገወጥ መሬት ሽያጭ ውል ስለመኖሩ በአግባቡ በጭብጥነት ተይዞ በማስረጃ አጣርቶ ክርክር ሳይደረግበት ወደ ነበሩበት ይመለሱ በማለት የተሰጠው ውሳኔና የተደረሰበት ድምዳሜ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 182(2) ያላገናዘበ ነው፡፡ በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሻሽሏል፤ ይ/ባይ ህውከት ፈጠሩብኝ በማለት ያቀረቡት የህውከት ይወገድልኝ አቤቱታ ውድቅ ተደርጓል፤ የስር ፍ/ቤት ግራ ቀኙ ወደ ነበሩበት ይመለሱ በማለት የሰጠው ውሳኔ አቤቱታ ባልቀረበበት ጉዳይ እና የክርክሩ ጭብጥ ባልሆነበት ጉዳይ የተሰጠ በመሆኑ ተሽሯል በማለት ወስኗል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች በቀን 06/05/2013 ዓ/ም ባቀረቡት ማመልከቻ ተፈፀመ የሚሉትን ስህተት ዘርዝረው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ተጠሪዎች እየፈጠሩ ያለውን ሁከት ያቁሙ ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ግራቀኙ የስር ክርክራቸውን በማጠናከር መልስና የመልስ መልስ ተለዋውጠዋል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ሁለቱም ወገኖች ያቀረቡትን ክርክር፤ ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የስር ፍርድ ቤቶች ባሳለፉት ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

ከክርክሩ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች ባቀረቡት ክስ ተጠሪዎች ምንም አይነት መብት ሳይኖራቸው ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ በይዞታየ ላይ በሃይል የተደገፈ ሁከት እየፈጠሩብኝ ስለሆነ የፈጠሩት ሁከት እንዲወገድ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው አከራካሪው ይዞታ በእኛ እጅ የሚገኝ ራሳችን የምናስተዳድረው ነው፤ አመልካች ይዞታውን በእጁ አድርጎ የሚያስተዳድረው አይደለም፤ በይዞታው ላይ ከህግም ይሁን ከውል የመነጨ መብት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት ከፍ ሲል እንደተገለፀው አመልካች ይዞታውን በሽያጭ ውል ከ1ኛ ተጠሪ ያገኙ መሆኑ በአመልካች ምስክሮች ተረጋግጧል፤ ውሉም ህገወጥ በመሆኑ ፈራሽ ነው፤ ህገወጥ በሆነ ውል አማካኝነት የተቀባበሉትን በፍ/ብ/ህ/ቁ 1815(1) መሰረት በመመላለስ ከውሉ በፊት ወደ ነበሩበት ሁኔታ ሊመለሱ ይገባል፤ ተጠሪዎች በህገ ወጥ ውል ያስተላለፉትን መሬት መያዛቸው የሁከት ተግባር አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በበኩሉ ውሳኔውን አሻሽሎ አመልካች በእውነት ሊያዝበት የሚችል የራሱ ይዞታ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ባለመቅረቡ ሁከት ይወገድልኝ በማለት አቤቱታውን ሊያቀርቡ አይችልም፤ ህውከት ፈጠሩብኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤ ነገር ግን የስር ፍ/ቤት ባልተጠየቀ ዳኝነትና ከክርክሩ ውጪ የውሉን ጉዳይ ተመልክቶ ግራ ቀኙ ወደ ነበሩበት ይመለሱ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል በማለት ወስኗል፡፡

በመሰረቱ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ሊቀርብ የሚችለው በይዞታው በእውን በሚያዘው ሰው ሰላማዊ የይዞታ አጠቃቀም ላይ ችግር ወይም መሰናክል ሲፈጠር ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1140 እና 1149 ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ መልኩ ለቀረበው ክስ የሚሰጠው ዳኝነትም የተነሳው ህውከት እንዲወገድ እንዲሁም ስለደረሰ ጉዳት ኪሳራ እንዲከፈል ሊሆን ይችላል፡፡ በተለይ ተከሳሽ አድራጎቱን የሚፈቅድ መብት እንዳለው በፍጥነትና በማይታበል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓይነት ካላስረዳ በቀር ህውከቱ እንዲወገድ እንደሚታዘዝ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1149(3) ሥር ተመልክቷል፡፡ በአንፃሩም ሁከቱን ፈጠረ ከተባለው ሰው ጋር የተደረገ በውል ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ካለ ግንኙነቱ የሚገዛበት የውልና የህግ አግባብ ተለይቶ ራሱን ችሎ ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በአከራካሪው ይዞታ አመልካች በእውነት ሊያዝበት የሚችል የራሱ ይዞታ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያልቀረበ ስለመሆኑ ፍሬ ነገርን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን በህግ ስልጣን በተሰጣቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ህውከት ይወገድልኝ ተብሎ የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲሆን መወሰኑ ከፍ ሲል የተመለከተውን የህጉን ይዘትና መንፈስ የተከተለ በመሆኑ የህውከት ይወገድልኝ ክሱን ውድቅ በማድረግ ረገድ የተላለፈው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር አድርገውታል የተባለው የሽያጭም ሆነ ሌላ ውል ህጋዊነት እንዲሁም ውል ፈርሶ ግራቀኙ ከውሉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን ከህውከት ክሱ ጋር ተያይዞ ዳኝነት እንዲሰጥበት የቀረበ አቤቱታ ባለመኖሩና በውል ላይ የተመሰረተው ግንኙነት ይኸው በሚገዛበት የውልና የህግ አግባብ እራሱን ችሎ ሲጠየቅ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚገባ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ከተጠየቀው ዳኝነት በማለፍ ያሳለፈው ውሳኔ ክርክሩ የሚመራበትን ስርዓት እና ከላይ የተጠቀሱትን የህጉን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የተከተለ ባለመሆኑ ውሳኔው በዚህ ረገድ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መታረሙ በአግባቡ ነው፡፡

በአጠቃላይ ይግባኝ ሰሚው የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያሳለፈው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 16162 በቀን 08/04/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካች ህውከት ይወገድ በሚል ያቀረቡት ክስ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው፡፡

3. በአንፃሩ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ አደረጉ የተባለውን ውል በተመለከተ አቤቱታ ሲቀርብ የውል ግንኙነቱ ከሚገዛበት የውልና የህግ አግባብ አንፃር ታይቶ ዳኝነት ሊሰጥበት ከሚገባ በቀር አመልካች ካቀረቡት የሁከት ይወገድልኝ የዳኝነት ጥያቄ ጋር ተያይዞ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰጠቱ የተጠየቀውን ዳኝነት እና ህጉን የተከተለ አይደለም ብለናል፡፡

4. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

https://t.me/ethiopianlegalbrief



**ስሜ በተራ ቁጥር 3ኛ ላይ የምገኘው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን እንደምከተለው አስቀምጫለሁ**

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጡት ውሳኔ ላይ የአሁን አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ሲሆን በስር ፍ/ቤት በነበረው ክርክር የአሁን አመልካች በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ የአሁን ተጠሪ በመሬት ይዞታዩ ላይ ሁከት ስለፈጠረብኝ ሁከት ያቁምልኝ ሲል ጠይቋል፡፡ የአሁን ተጠሪም የፈጠርኩት ሁከት የለም ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም አከራክሮ የአሁን አመልካች ክስ ያቀረበበት የመሬት ይዞታ ከተጠሪ በሽያጭ ውል አግኝቻለሁ የሚል በመሆኑ የአሁን አመልካች በህገ መንግስቱ የተከለከለውን የመሬት የሽያጭ ውል መሰረት አድርጎ አግኝቻለሁ በሚለው የመሬት ይዞታ ላይ ሁከት ተፈጥሮብኛል ሲል የሁከት ክስ ሊያቀርብበት የማይችል ስለመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 36645 በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት በህገ ወጥ መንገድ ያዝኩ በሚለው መሬት የሁከት ክስ ሊያቀርብበት አትችልም፡፡ እንዲሁም ህገ ወጥ ውል በክርክርነት የቀረበ እንደሆነ ሌላ ክስ ማቅረብ ሳያስፈልግ በተያዘው የሁከት ክስ መዝገብ ላይ ተቀባይነት እንደሌለው መወሰን እንደሚቻል የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 79394 ላይ በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም የአሁን አመልካች በሽያጭ ውል ይዣለሁ ሲል ያቀረበው የሁከት ክስ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ክሱ ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔን እንደተገነዘብኩት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉምን መሰረት በማድረግ የአሁን አመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ክፍል ተገቢ ሆኖ፣ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ሲል የሰጠው ውሳኔ ክፍል ግን ሊታረም የሚገባው ጉዳይ ነው እላለሁ፡፡ ምክንያቱም የመሬት ሽያጭ ውል በህገ መንግሰቱ የተከለከለ ህገ ወጥ ውል ነው፡፡ የመሬት ሽያጭ ውል ከመጀመሪያውኑ እንደውል የማይቆጠር ፈራሽ ውል በመሆኑ በቀረበው የሁከት ክስ ክርክር ውሉ ተቀባይነት እንደሌለው ውሳኔ ሲሰጥ በህገ ወጥ ውሉ ካለ አግባብ ብልጽጓል የሚል ወገን ካለ በዚሁ አግባብ ከመጠየቅ በቀር ህገ ወጥ የመሬት ሽያጭ ውል በፍርድ ቤት ውሳኔ ፈራሽ እንደተደረገ ተወስዶ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ በሚል ውሳኔ መስጠቱ ህጋዊ መሰረት ያለው አይደለም፡፡ ሌላው የአሁን አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም አከራክሮ በሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካች ላቀረበው የሁከት ክስ ይዞታው በእጁ የነበረ ስለመሆኑ አላስረዳም፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባልተጠየቀ ዳኝነት ስለ ውል ጉዳይ አንስቶ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ ባለመሆኑ ሊታረም ይገባል ብሎ በውጤት ደረጃ የፌደራል የመጀሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማስረጃ የመስማትና የመመዘን በተሰጠው ሥልጣን አንጻር የአሁን አመልካች ክስ ያቀረበበት የመሬት ይዞታ በእጁ ያልነበረ መሆኑን አረጋግጦ ሁከት የለም ብሎ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ክስ ያቀረበበትን የመሬት ይዞታ ከአሁን ተጠሪ ላይ በሽያጭ ውል የገዛው ስለመሆኑ በማስረጃ ያረጋገጠ በመሆኑና የመሬት ሽያጭ ውል በህገ መንግስቱ የተከለከ ስለሆነ ከመጀመሪያውኑ ፈራሽ በመሆኑ የውል ይፍረስልኝ ክስ ማቅረብ ሳያስፈልግ በተያዘው መዝገብ ላይ ሕገ ወጥ ውሉን ውድቅ ማድረግ እንደሚቻል የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 79394 ላይ በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት የአሁን አመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ስህተት ያልተፈጸመበት ሆኖ እያለ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የህገ ወጥ የመሬት ሽያጭ ውል ከክርክራቸው ውጪ ነው ሲል የሰጠው እርማት ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም መጀመሪያውኑ የአሁን አመልካች ክስ ማቅረብ መቻል የሚገባውና ይህን ባላሟላበት ይዞታው በማን እጅ ነበር ወደ ሚለው ጉዳይ ማለፍ አስፈላጊም ስለማይሆን ነው፡፡ ይህም ሆኖ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ከላይ በተገለጸው መሰረት እርማት በማድረግ በውጤት ደረጃ ክሱ ውድቅ መደረጉን ማጽናት ሲገባ የመሬት ሽያጭ ውል መጀመሪያ በፍርድ ቤት ውሳኔ ፈራሽ መደረግ ነበረበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሚል ምክንያታዊ እርማት ውሳኔ መስጠቱ እንደ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ህገ ወጥ የመሬት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ ክስ ሊቀርብ ይገባል ብሎ ውሳኔ መስጠት የመሬት ሽያጭ ውል ከመጀመሪያውኑ ፈረሽ መሆኑ እየታወቀ ካለአግባብ እንደገና ግራ ቀኙን ለሌላ ያልተገባ ክርክር የሚጋብዝ፣ ላልተገባ ወጪ እና ተጨማሪ ጊዜ ብክነት የሚዳረግ፣ ህገ ወጥ የመሬት ሽያጭ ውልን እውቅና የሚሰጥ፣ የራሱን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 79394 ላይ የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም የሚጻረር፣ የውል መሰረታዊ መርሆን የሚጻረር እና የፌደራል ህገ መንግስትን የሚጻረር ውሳኔ ስለሚሆን ተገቢነት ያለው ውሳኔ አይደለም እላለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም